# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 44 ግንቦት 29 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

# ሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ



## ነፃ ሀሳብ

# ሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ

እያሱ መኮንን

## የሰብዓዊ መብቶች ምንድን ናቸው?

ሰብዓዊ መብቶች የሰው ልጆች መሰረታዊና እንደ ሰው ለመኖር የሚያስፈልጋቸው መብቶችን የሚያጠቃልል ነው:: ሰብዓዊ መብቶች ሁሉም ሰዎች በተፈጠሮ (ሰው በመሆናቸው ብቻ) የሚጎናጸፉቸው መሰረታዊ መብቶች ሲሆኑ እነዚህ መብቶች በማንኛውም ዓይነት መንግሥታዊም ሆነ ሌላ ኃይል ሊነጠቁ ወይም ሊገደቡ አይገባም:: ስለዚህም ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ እነዚህን መብቶች ያለ ማንም ችሮታና ስጦታ በተፈጥሮ በነጻ ማግኘት አለበት::እነዚህ መብቶች ዘር፡ ቋንቋ፡ ጎሳ፡ ሃይማኖት፡ ጾታ፡ ወይም ሌሎች ልዩነቶች ሳይገድባቸውና ሳይለዩ ሁሉም ሰዎች እኩል የሚያገኛቸው መብቶች ናቸው::እነዚህን መብቶች ለመጠየቅና ለመጠቀም ሰው ሆኖ መፈጠሩ ብቻውን በቂ ነው::

የሰበአዊ መብቶች መጠበቅ ዓላማ የሰውን ልጅ መሰረታዊ መብቱ ተጠብቆ ክብሩና ጥቁሙ እንደ ሰው እንዲከበርለት ለማድረግ የሚያገለግሉ ናቸው:: ስለዚህም እነዚህ መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ከሰው ልጅ ተፈጠሮአዊ ክብርና ጥቅም ተለይተው ሚታዩ አይደሉም:: እነዚህ መሰረታዊ የሰው ልጅ መብቶች ከአንድ አካል በችሮታ ለሌላ አካል የሚበረከቱ ወይም በተፈለገ ጊዜ የሚነጠቁ ሳይሆኑ መንግሥት ሁል ጊዜ የመጠበቅና የማስጠበቅን ግዴታ የሚጥሉ ናቸው::

### የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የሚደረጉ ትግል አመጣጥ

የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ ለረጅም ዘመናት ትግል ሲካሄድበት ቆይቷል:: አሁንም በዚህ ዘመን እየተካሄደበት ይገኛል:: በተለይም ከ1789 የፈረንሳይ አብዮት በኋላ የሰውን ልጅ መሰረታዊ መብቶች እንዲከበሩ እልህ አስጨራሽ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ንቅናቄዎችና አብዮቶች ተካሂደዋል:: ሰዎች እነዚህ መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች



እነዲከበሩላቸው ሞትና የአካል ጉዳትን ጨምሮ የተለያዩ እልህ አስጨራሽ ትግል አካሂደዋል:: መንግሥታት እነዚህን ሰብዓዊ መብቶች ለማክበር በአብዛኛው የሚፈልጉ ባለመሆናቸው መንግሥታትን ለማስገደድ ግለሰቦችና ቡድኖች መስዋእትነት እንዲከፍሉ አስገድዷቸዋል:: ከነዚህ ወሳኝ ዓለም አቀፋዊ ትግሎች መካከል፡-

1. የፈረንሳይ አብዮት- የፈረንሳይ አብዮት ሁሉም ፈረንሳዊ የመኖር፡ በህግ ፊት እኩል የመታየት፡ እና የመከባበር መብቶች እንዲከበሩ የተደረገ ትግል ነው:: የዚህ ትግል ውጤቶችም በአሁኑ ሰዓት የፈረንሳይ
2. ዋነኛ የሰብዓዊ መብቶች መሰረት ናቸው::ይህ ትግል ለሌሎች ሰብዓዊ መብት መከበር የሚደረጉ ትግሎች ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል::
3. የጸረ- ባርነት ትግል-ይህ በተለይም ነጮች በጥቁሮች ላይ ለዘመናት ያደረሱትን ዘግናኝ ጭቆና ለመታገልና እንደ ሰው ለመቆጠር የተደረገ እልህ አስጨራሽ የመቶ ዓመታት ትግል ነው::በዚህ ትግል በተለይ ጥቁሮች ከሌላው የሰው ዘር እኩል መብት እንዲኖራቸው ያደረጉትና እያደረጉት ያሉት እጅግ ረጅምና እልህ አስጨራሽ እንቅስቃሴ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የሚደረገው ትግል ምን ያህል ረጅም ሥራ እንደሚጠይቅና መራር እንደሆነ ጉልህ ማሳያ ነው::
4. የጸረ- ቀኝ አገዛዝ ትግል-ይህ ትግል ሀገራት በተለይም ከአውሮፓውያን ቀኝ አገዛዝ ለመገላገል ያደረጉት ትግልን የሚያመለክት ነው:: በተለይም አፍሪካውያንና ደቡብ አሜሪካውያን ራሳቸውን ከቀኝ ገዢዎች ለማላቀቅ ያደረጉትን ብርቱ ትግል የሚያስታውስ ነው:: በዚህም ሀገራት ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደርና በሀገራቸው ሀብት የበይ ተመለካች እንዳይሆኑ ለማድረግ ያደረጉትን ትግል ያጠቃልላል ::

### በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች

መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ዝርዝር በቁጥር እጅግ ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋና ተብለው የሚቆጠሩት ግን የሚከተሉትን ያጠቃልላል::

1. የእኩልነት መብት- ሰው ሁሉ በህግ ፊት እኩል መብትና ግዴታ እንዳለበት የሚያመለክት ነው::
2. የመኖር መብት- የሰው ልጅ የመኖር መብቱ ሁል ጊዜ ሊጠበቅለት እንደሚገባ እና በማንም የማይነጠቅ መሆኑን የሚያመለክት ነው::
3. የማሰብና የመናገር መብት- የሰው ልጅ የማሰብና ሀሳቡን ያለማንም ተጽእኖ በነጻነት የመናገር መብቱን የሚያመለክት ነው::
4. የእምነትና እምነትን በጋራ የማካሄድ መብት- ይህ መብት የሰው ልጅ መሰረታዊ መብት ሲሆን አንድ ሰው የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል፣ከፈልገው ሰው ጋር በመሆን እምነቱን የማራመድና የመስበክ መብቱን የሚጠብቅ ነው::
5. ከአካላዊ ጥቃት የመጠበቅ መብት- የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ብቻ መላ ሰውነቱ ከማንኛውም ጥቃት የመጠበቅና ጥቃት እንዳይደርስበት የመከላከል መብት አለው::

### የሰብዓዊ መብቶችና የዓለም አቀፍ ህጎች

የሰብዓዊ መብቶች በዋና ዋና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ በስፋት ተደንግገው የሚገኙ ናቸው:: የዓለም አቀፉ የሰብዓዊ ▶



▶ መብቶች ድንጋጌዎች (UDHR) በ1948 ሲደነገግ በዋናነት እነዚህን የሰብዓዊ መብቶች በሁሉም የዓለም ሀገራት ዘንድ በእኩል እንዲከበሩ ለማድረግ ታስቦ የወጣ ነው:: ይህ ድንጋጌ በአሁኑ ሰዓት በአብዛኛው የዘመናዊ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ መነሻና ማጣቀሻ ነው::

በመቀጠልም የዓለም አቀፉ የሰብዓዊ ዴሞክራሲያዊና ፖሊቲካዊ መብቶች የቃል ኪዳን ሰነድ (ICCPR) ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ ሀገሮች ጸድቆ ወደ ሥራ ገብቷል:: ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ የሰዎች የሰብዓዊ፣ዴሞክራሲያዊና ፖሊቲካዊ መብቶች እንዲከበሩ የሚያስገድድ ድንጋጌዎችን የያዘ ሰነድ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞም የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶችን የሚያስጠብቀው (ICESCR) የቃል ኪዳን ሰነድ ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ ሀገራት ጸድቆ ወደ ሥራ ገብቷል:: ይህ የቃል ኪዳን ሰነድ ሰዎች የተሟላ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሰብዓዊ፣ዴሞክራሲያዊና ፖሊቲካዊ መብቶች ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶችም አብረው መጠበቅ አለባቸው በማለት የወጣ ሰነድ ነው ::

### የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ

አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት በውስጡ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ይዟል :: ሕገ መንግሥቱ በመግቢያው ላይ በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡ ዓላማዎችን ለማሳካት የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበር እንደ ግዴታና ቅድመ ሁኔታ አስቀምጦታል:: እንዲሁም የሕገ መንግሥቱ ሲሶ(1/3) ክፍል መሰረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ የሰፈረበት ነው።።በተጨማሪም ሕገ መንግሥቱ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የቃል ኪዳን ሰነዶች እንደ ኢትዮጵያ ሕግ እንደ ሚቆጠሩና በቀጥታ ተፈጻሚነት እንደሚኖራቸው የሚገልጽ ነው:: በሕገ መንግሥቱ መንግሥትና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት መሰረታዊ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች እንዲከበሩ የማድረግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል:: ይህን የማክበርና የማስከበር ግዴታም በሁሉም ደረጃ ባሉ የፌደራልና የክልል መንግሥታት ላይ የሚወድቅ ነው::

ከዘህ በተጨማሪም ሕገ መንግሥቱ በስሩ የተደነገጉትን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል እጅግ አስቸጋሪ የሆነ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ መንገድን መከተል እንዳለባቸው ይደነግጋል:: ይህም ማለት አንድን የሕገ መንግሥቱን የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ ለማሻሻል ሁሉም ኢትዮጵያ ክልሎች እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን የፌዴሬሽን ምክር ቤት በ3/2 ድምጽ ማጽሰቅ ይጠበቅበታል::ይህም የሕገ መንግሥቱ የሰብዓዊ መብት ክፍል ተጠብቆ እንዲቆይ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው::

### የሰብዓዊ መብት ገደቦች

ከላይ በግልጽ እንደተቀመጠው ሰብዓዊ መብቶች የሰው ልጆች መሰረታዊና እንደ ሰው ለመኖር የሚያስፈልጋቸው መብቶች ቢሆኑም እነዚህ መብቶች ምንም ዓይነት ገደብ የላቸውም ማለት አይደለም:: እነዚህ ሰብዓዊ መብቶች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ብቻ ተገቢው ገደቦች ሊቀመጥባቸው ይችላል:: ለምሳሌ በሕይወት የመኖር መብት ሰብዓዊ መብት ቢሆንም በአንዳንድ ከባድና ዘግናኝ ወንወጀሎች በመፈጸሙ አንድ ተከሳሽ ቢፈረድበት በሞት ሊቀጣ መቻሉ ሰብዓዊ መብቱን እንደመግፈፍ አያስቆጥርም:: በሌላም በኩልም የመናገርና የማሰብ መብት ሳይሸራረፍ መከበር ያለበት ቢሆንም ይህ መብት ግን ለምሳ ሌሌሎችን በሰላም የመኖር መብት ለማፍረስ ወይም ሰውን በሀሰት ለመወንጀል የሚውል ከሆነ ገደብ ሊደረግበት ይችላል::በተጨማሪም እምነትን በነጻነት የማራመድ መብት የተከበረ ቢሆንም ይህ ግን ሌሎችን እምነቶች ለማንቋሸሽና ለማዋረድ የሚጠቀምበት ከሆነ ገደብ ሊጣልበት ይችላል::ስለዚህ ለሉም መብቶች ከሞላ ጎደል የራሳቸው የቻለ ህጋዊና ተመጣጣኝ ገደቦች ሊቀመጥባቸው ይችላል::ሰብዓዊ መብት እንደማንኛውም ሌላ መብት ሁሉ የራሱ ገደብ ያለበት እንጂ ያለ ምንም ገደብ የሚሰጥ ልቅ መብት አይደለም:: የሙያው አጥኚዎች የአንድ ሰው መብት የሚያቆመው የሌላው ሰው መብት በሚጀምርበት ቦታ ላይ ነው ይላሉ::

የሰብዓዊ መብት አፈጻጸም በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል በሌላ ጊዜ የምንመለስበት ይሆናል::

የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ በሚከተለው የኢሜይል አድራሻቸው በኩል ማግኘት ይቻላል :- eyosimm@gmail.com


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ግንቦት 29 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የኢዜማ የሥራ አስፈሚቴ መደበኛ ስብሰባ እየተካሄደ ነው



**የሀገራችንን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታና ኢዜማ ወደፊት ሊወስዳቸው ስለሚገቡ አቅጣጫዎች ላይ ይመከራል**

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የሀገራችን አጠቃላይ ፖለቲካዊ ሁኔታ እና የወደፊት የፓርቲውን አማራጭ አቅጣጫዎች በዝርዝር የሚፈትሽ ውይይት እያደረገ ነው። የ2 ዓመቱ የለውጥ ሂደት፣ የኢዜማ የአንድ ዓመት እንቅስቃሴ እና የወደፊት አቅጣጫዎች በውይይቱ ላይ በስፋት የሚዳሰሱ ጉዳዮች እንደሆነ ከፓርቲው ጽሕፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

በውይይቱ ላይ ከኢዜማ ሥራ አስፈጻሚ አባላት እና በተለያዩ ዘርፎች ያሉ ቋሚ ኮሚቴዎች አባላት እንዲሁም የፖሊሲ ጥናት ባለሙያዎች እየተሳተፉበት ሲሆን ሀገራችን ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ እና ከኢዜማ የአንድ ዓመት እንቅስቃሴዎች ተሞክሮዎች በመነሳት ወደፊት ፓርቲው ሊከተለው ስለሚገባ አቅጣጫ የሚተነትኑ ጽሑፎች የሚቀርቡበት ነው። በተመሳሳይም ከፓርቲው ውጭ ያሉ ገለልተኛ የፖለቲካ ተንታኞችም በሀገራችን ሁኔታ እና በኢዜማ የአንድ ዓመት ጉዞ ላይ ያላቸውን ምልከታ ለተወያዮች የሚያቀርቡ ይሆናል።

በውይይቱ ላይ በመመስረት የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ መሻሻል የሚገባቸው እና ጠንካራ ጎኖችን በመለየት የፓርቲው የሚከተለው የወደፊት አቅጣጫ ላይ ውሳኔዎችን ያሳልፋል ተብሎ ይጠበቃል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የተመሰረተበትን አንደኛ ዓመት ባለፈው ግንቦት 1 እና 2 ቀን 2012 ዓ.ም ያከበረ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ 435 የምርጫ ወረዳዎች ላይ አባላትን አደራጅቶ መዋቅር የዘረጋ እና ከ40 በላይ አማራጭ የፖሊሲ ሰነዶችን በባለሙያ እያዘጋጀ የሚገኝ ዜግነትን መሠረት ያደረገ ፖለቲካ እና ማኅበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን የሚሠራ የፖለቲካ ፓርቲ ነው።



# መንግሥት ለዜጎች ደህንነት እና ሰብዓዊ መብቶች መጠበቅ እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያለውን ቁርጠኝነት እንዲያረጋግጥ ኢዜማ ጠየቀ

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች አምነስቲ ኢንተርናሽናል«ሕግን ከማስከበር ባሻገር» በሚል ርዕስ ያወጣውን መግለጫ ተከትሎ ግንቦት 25 ቀን 2012 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ለሚያደርገው ልዩ ምርመራ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ እና በምርመራው ውጤት ላይ በመመስረትም አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ በመውሰድ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ቁርጠኝነቱን እንዲያረጋግጥ አሳሰበ፡፡

ፓርቲው ግንቦት 25 ቀን 2012 ዓ.ም በማኅበራዊ ድሕረ ገፁ ላይ ባወጣው መግለጫ አምነስቲ የዘረዘራቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ጉባዔ ካወጣቸው ዘገባዎች ጋር እንደሚመሳሰል ጠቅሶ ዘገባውን በሚመለከት አስተያየታቸውን ሲጠየቁ አስተያየታቸውን ያልሰጡ የፌደራልና የክልል መሥሪያ ቤት ተቋሞችን ተችቷል፡፡ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ምላሽ የሰጠ ብቸኛ የመንግሥት ተቋም ለሆነው የአማራ ክልል ሰላም እና ደህንነት ግንባታ ቢሮ ኢዜማ አክብሮቱን ገልጿል፡፡ ‹‹በሁሉም ደረጃ ያሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በተሰማሩበት የኃላፊነት ዘርፍ የተከሰቱ ችግሮችን በተመለከተ የሚቀርብላቸውን የማብራሪያ ጥያቄዎች በቀናነት መቀበል እና ምላሽ መስጠት ግዴታቸው እንደ ሆነ እናምናለን።የሚቀርቡ ጥያቄዎችን በርን ክፍት አድርጎ መቀበል እና ግልጽነት የተሞላው ምላሽ መስጠት፣እንዲሁም የተሠሩ ስህተቶችን ለማረም ዝግጁ መሆን በሂደት ለምንገነባው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ እሴቶች ናቸው›› ሲል ፓርቲው ማሳሰቢያውን ሰጥቷል፡፡ ከሰብዓዊ መብት ጋር በተያያዘም የፌደራል መንግሥቱም ሆነ በሌላ ደረጃ የሚገኙ የመንግሥት አካላት ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ምላሽ መስጠት እንደሚጠበቅባቸውና ግዴታቸው ጭምር እንደሆነ ኢዜማ ጠቁሟል፡፡

የአምነስቲ ዘገባ ውስን ክስተቶች ላይ ያጠነጠነ ነው ያለው ኢዜማ፣ የዓለም አቀፉ ሰብዓዊ መብት ተሟጋች ዘገባ የዜጎች ስም፣የተፈጸመበት ቦታ እና ጥሰቱን እንደፈጸሙ የተጠቀሱት ተቋማት በግልጽ በመቀመጣቸው የመረጃውን ትክክለኛነት ለማጣራት ቀላል ነው ብሏል፡፡ ‹‹ተጨማሪ ምርመራ ተደርጎ የተጠቀሱት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መፈጸማቸው ከተረጋገጠ የእርምት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ከበቂ በላይ አመላካች ናቸው›› በማለት ፓርቲው በተጨማሪ ምርመራ ተፈፅመዋል የተባሉት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መፈፀማቸው ከተረጋገጠ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስቧል፡፡የማረጋገጡን ሥራ በሚመለከት ኢዜማ፣ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን አስፈላጊ የሚባለውን ድጋፍ ተደርጎለት የማጣራት ሥራ እንዲያካሄድ እና የደረሰበትን ውጤትም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለክልል ምክር ቤቶች እና ለሕዝብ ይፋ እንዲያደርግ ጥያቄውን አቅርቧል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር የሆኑት ዳንኤል በቀለ (ዶ/ር) የአምነስቲን መግለጫ ተከትሎ ከሸገር ሬዲዮ ጋር ባደረጉት ቆይታ ተቋሙ ተአማኒነት ያለው ሪፖርት በመሥራት የሚታወቅ መሆኑን ጠቅሰው ተቋሙ አገኘኋቸው ያላቸውን ግኝቶች በተገቢው የኃላፊነት ስሜት ተቀብሎና አጣርቶ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡ ግኝቶቹን ሙሉ ለሙሉ ውድቅ ማድረግ ትክክለኛ አካሄድ አይደለም ያሉት ኮሚሽነሩ ለሪፖርቱ አሠራር ግን ተገቢ ትችት ማቅረብ ይቻላል ብለዋል፡፡ መንግሥት፣ አምነስቲ በማስረጃ ጭምር ያረጋገጠውን እንደ አሳሳቢ መረጃ ወስዶ ተገቢውን እርምት ለመውሰድ መዘጋጀት ያስፈልገዋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡የኢፌዴሪ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ የሆኑት አዳነች አቤቤ በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው ባስተላለፉት መልዕክት በአምነስቲ ኢንተርናሽናል የወጣውን መግለጫ መመልከታቸውን ጠቅሰው የማጣራት ሥራ እንደ ጀመሩ ተናግረዋል፡፡ በማጣራት ሥራቸው በሚገኘው ውጤት፣ ዘገባው እውነት በሆነበት ልክ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃ እንወስዳለን ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የዜጎች ሰብዓዊ መብት መከበር በምንም ምክንያት እና በማንኛውም ጊዜ ለድርድር የማይቀርብ መሆኑን በመግለጫው የጠቀሰው ኢዜማ፣ዜጎች ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚያደርሱ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ መገንባት ለሚያስፈልገው ዴሞክራሲያው ሥርዓት ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው በመጥቀስ መንግሥት ለዜጎች ደህንነት እና ሰብዓዊ መብቶች መጠበቅ እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያለውን ቁርጠኝነት እንዲያረጋግጥ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ለሚያደርገው ልዩ ምርመራ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ እና በምርመራው ውጤት ላይ በመመስረትም አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ በመውሰድ ቁርጠኝነቱን ያረጋግጥ ሲል ጥያቄውን አቅርቧል፡፡

ፓርቲው በመግለጫው መደምደሚያ ላይ ‹‹የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም የሰብዓዊ መብት ጥሰትን እና በየጊዜው የሚከሰቱ ጉዳዮችን ሰበብ በማድረግ የሀገር መረጋጋትን እና ሰላምን እንዲሁም የዜጎችን ደህንነት አደጋ ውስጥ ሊጥል ከሚችል የፖለቲካ ትርፍን ዓላማ ካደረገ ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዲታቀቡ አጥብቀን እንጠይቃለን›› በማለት መሰል አጋጣሚዎችን ለፖለቲካ ትርፍ ከማዋል ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲታቀቡ ጠይቋል።

# ኢዜማ ፖሊሲዎቹን በመከለስ ላይ ይገኛል




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የመንግሥትና የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪ የሆኑት አማንይኹን ረዳ የኮሮና ወረርሽኝ ተከትሎ ኢዜማ አስቀድሞ ቀርጿቸው የነበሩ ፖሊሲዎቹ ላይ ክለሳ እያደረገ እንደሆነ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

ኢዜማ፣ በየጊዜው ያሉ ተለዋዋጭ የሆኑ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ከግምት በመከተት ፖሊሲዎቹን ሲቀርፅ እንደ ነበር የገለፁት አማን ይኹን፣ ከኮሮና ወረርሽኝ በተጨማሪ የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ፣ ከፍተኛ የሆነ የሥራ አጥነት ችግር፣ በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ የሚመጣ ድርቅ፣ በአውሎ ንፋስም ሆነ በሌሎች ተፈጥሮዊና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ ሊመጡ የሚችሉ መጠነ ሰፊ የሆኑ የማኅበረሰብ ቀውሶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ፖሊሲዎቻችን እነዚህን ከግምት ከተዋል ወይ?ተቋማዊ አቅም ከመገንባት አንፃርስ ፖሊሲዎቻችን ምን መደረግ እንዳለበት ያትታሉ?የሚለውን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ፓርቲያቸው ስላገኘው ፖሊሲዎቹን ለማሻሻል እየሠሩ እንደ ሚገኙ የፖሊሲ ጉዳዮች አስተባባሪው ጠቁመዋል፡፡

የኮሮና ወረርሽኝ መከሰት ተከትሎ ሀገር አቀፉ ምርጫ መራዘሙ ተጨማሪ ጊዜ እንደሰጣቸው የሚናገሩት አማንይኹን ረዳ፣ በዚህ ጊዜ ውስጥም እያንዳንዱን ፖሊሲዎቻቸውን ለማሻሻል፣ ተጨማሪ ባለሙያዎችንም ሆነ እያንዳንዱን ባለድርሻ አካላትን ለማሳተፍና ለማወያየት እድል እንደፈጠረላቸው ተናግረዋል፡፡ በቀረፃ ሂደት ላይ ያሉት ፖሊሲዎችንም በዘርፉ ባለሙያዎች በሆኑ ምሁራን እያስተቿቸው እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

ኢዜማ፣ የኢትዮጵያን ችግር በሂደት ይፈቱልኛል፤ ዜጎች የተሟላ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባለቤትና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላሉ፤ ሁለንተናዊ፣ መሰረተ ሰፊና ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደርግ የምጣኔ ኃብት ዕድገትና ልማት ለማምጣት ይረዳሉ፤ ማኅበራዊ ፍትህ ለማስፈን፤ ዘላቂ ልማትና ዋስትና ያለው ሰላም ለማረጋገጥ፣ እንደዚሁም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ-መንግሥትን በኢትዮጵያ ዕውን ለማድረግ ይረዳሉ ብሎ ያመነባቸውን 45 የፖሊሲ ሰነዶችና በሂደትም ፖሊሲዎቹን ለማስፈፀም የሚረዱ ስልቶች (strategies) ቀረፃ እያደረገ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

## የኢዜማ ምክትል ሊቀመንበር መፅሐፍ አሳተሙ



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)ምክትል ሊቀ መንበር ጫኔ ከበደ (ዶክተር) «የዘር ፖለቲካና የቋንቋ ፌደራሊዝም በኢትዮጵያ»በሚል ርዕስ መጽሐፍ ማሳተማቸውን ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

መጽሐፉ የጥናታዊ ጽሑፍ ቅርፅ ይዘት እንዳለው የጠቆሙት ጫኔ ከበደ፣ በውስጡ ብዙ መረጃዎችን አካቶ እንደያዘ ገልፀዋል፡፡ የኢትዮጵያን ወረዳዎችና ዞኖች ሁሉ ያካተተና የሕዝቡ ቁጥራቸውን ትንበያም ያስቀመጠ መሆኑን ምክትል ሊቀ መንበሩ አስረድተዋል፡፡ በየወረዳው እና ዞኖች የሚገኙ ብሔረሰቦች ቁጥር ስብጥርንም ያካተተና የኢትዮጵያን ስነ-ሕዝብ የሚያመላክትም መሆኑን ምክትል ሊቀ መንበሩ ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፌደራሊዝም ምንድን ነው?አካታች የሚሆነው ፊዚካል ፌደራሊዝምስ ምንድን ነው?የሚሉ ሀሳቦችንም እንደዳሰሱበት ገልፀዋል፡፡ ምን ዓይነት ፌደራሊዝም ያዋጣል?በሚለው ዙሪያም የተለያዩ ጥናቶችን መመልከታቸውንና በመጽሐፋቸው መደምደሚያ ላይም ምክረ ሀሳብ ማስቀመጣቸውን አስረድተዋል፡፡ መጽሐፉ ሀሳብ ሊመነጭበት የሚችል መጽሐፍ ነው ያሉት ጫኔ ከበደ (ዶክተር) የመንግሥት አካላትም ሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች መጽሐፉን ቢያገኙት ጥሩ ግብዓት ይሆናቸዋል ብዬ አምናለሁ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

መጽሐፉ 15 ምዕራፎችን ይዞ በ390 ገፅ የተቀነበበ ሲሆን ዋጋው 200 ብር ነው፡፡ መጽሐፉን በጃፋር፣ ዩኒቨርሳል፣ ጦቢያ መጽሐፍት መደብሮች እንዲሁም በሜጋ አሳታሚ ድርጅት በኩል ደግሞ በየክልል ቅርንጫፎቹ ማግኘት ይቻላል፡፡ የኢዜማ ምክትል ሊቀ መንበር የሆኑት ጫኔ ከበደ (ዶ/ር) በሚቀጥለው ሳምንት የዜጎች መድረክ እትም በመፅሐፋቸው ዙሪያ ለመነጋገር እንግዳችን አድርገን ይዘናቸው የምንቀርብ ይሆናል፡፡



# < <የኮሮና ጉዳይ የአንድ ቡድን ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ዜጋ ጉዳይና ኃላፊነት ነው> > ገዛኸኝ ሀይሉ



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳደር በሰሜን ውሎ ዞን የቆቦ ምርጫ ወረዳ የኢዜማ ጽ/ቤት ጸሀፊ የሆኑት ገዛኸኝ ሀይሉ ሕብረተሰቡ ስለ ወረርሽኙ ያለው ግንዛቤ ማነስና መዘናጋት ሊያስከትለው የሚችለው ማኅበራዊ ቀውስ ያሳስበናል ሲሉ ለዜጎች መድረክ ገለፁ፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ የመጣው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በሀገራችንም መከሰቱ ከተረጋገጠበት ማግስት ጀምሮ በርካታ ዜጎችን በማጥቃት ላይ የሚገኝ ቢሆንም የአካባቢያችን ማኅበረሰብ ስለ ወረርሽኙ ያለው ግንዛቤ ማነስና ለመግለጽ በሚከብድ ሁኔታ እያሳየ ያለው ቸልተኝነትና መዘናጋት ሊያስከትለው የሚችለው ማኅበራዊ ቀውስ ያሳስበናል ያሉት ጸሐፊው፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወረርሽኙን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ የታወጀ ቢሆንም አዋጁን በትክክል ሊያስፈጽም የሚችል አካል ባለመኖሩ ኃላፊነት በጎደለው መልኩ የብልጽግና ፓርቲ ያለውን መንግሥታዊ የስልጣን መዋቅርን በመጠቀም በርካታ ሰዎች የሚታደሙበት ስብሰባዎችን እያካሄደ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ወረርሽኙ በሀገራችን መከሰቱ ይፋ በተደረገበት ወቅት በሕዝቡ ውስጥ የፈጠረው የፍርሀት ስሜት ከእለት ወደ እለት ወደ እለት እየተሸረሸረ ይደረጉ የነበሩ ቅድመ ጥንቃቄዎች ችላ ተብለው ‹‹ኮሮና የከተማ ፖለቲካ ነው›› ወደ ማለት በመደረሱ የሕብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ወደ ቀደመው ማኅበራዊ ሁኔታ ተመልሷል በማለት የጠቆሙት ገዛኸኝ ሀይሉ፣ የቫይረሱ የማኅበራዊ ስርጭት ከእለት ወደ እለት እያሻቀበ በመጣበት በዚህ ወቅት እንዲህ አይነት ኃላፊነት የጎደለው ተግባር መፈጸም ሕዝብን ከመናቅም በላይ በዚህ ሕዝብ ላይ የሚከሰተውን ብሎም የሚያሳርፈውን ማኅበራዊ ቀውስ አለመረዳት ነው ብለዋል።

ወረርሽኙን ለመቆጠጠርና ለመከላከል በቆቦ ከተማ የሚንቀሳቀሱ አገልግሎት ሰጪ የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች ላይ ብቻ እየተወሰደ ያለው ደንብ የማስከበር እንቅስቃሴ በሁሉም ዘርፎች ላይ መቀጠል አለባቸው ያሉት ገዛኸኝ ሀይሉ፣ የኮሮና ጉዳይ የአንድ ቡድን ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ዜጋ ጉዳይና ኃላፊነት በመሆኑ፤ ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ብልጽግና ፓርቲም ይሁን በምርጫ ወረዳችን የሚገኙ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከምን ግዜም በላይ ሕዝብን የመታደግ ኃላፊነት በላያችን ላይ በመውደቁ የፖለቲካ አመለካከቶቻችንን ወደ ጎን በመተው በጋራ እንድንሰራ እና ለሕዝባችን በአንድነት እንድንቆም ጥሪዬን አቀርባለሁ ሲሉ ጸሐፊው ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡።